# ስህተትን መደጋገም መብትንም ሀገርንም ያሳጣል

(ሐተታ ከፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምፅ ሬዲዮ)

ሕይወት ተመክሮ ነው:: ያሳለፍነው ጊዜና ያየነው ሁሉ ተመክሮአችን ነው:: ታሪክም ያስተምረናል:: ለዚህም ነው ታሪኩን የረሳ ስህተቱን ይደግማል የሚባለው:: ትምህርት መቅሰምን እምቢ ብሎ በጭፍኑ መጓዝን መርጧልና:: ስህተት በግለሰብ ደረጃ ከተወሰነ ጉዳቱ ቀላል ሊሆን ይችላል ግና በሀገር ጉዳይና የነገ ዕጣ ላይ ስህተት እየተፈፀመ ከሆነ ግን ሀገርንም እስከማጣት ሊያደርስ የሚችል ከባድ ጥፋት ሊሆን ይችላል::

ዛሬ የወያኔ አገዛዝ ሊቆጣጠረው እያቃተው ባለ ቀውስ ውስጥ እየገባ ባለበት ይህን ሁኔታ ተጠቅሞ ለመሰረታዊ ለውጥ መዋደቅ ሲገባ ያረጁ ያፈጁ ስህተቶች እየተፈፀሙ የሕዝብ ትግልና ድልም ላይ ጋሬጣ እየሆኑ ነው:: እስቲ ወደ ኋላ መለስ ብለን ያሳለፍነውን ጊዜ የሩቁን ባይሆን የቅርቡን እንገምግም:: በ1997 ሉ ምርጫ ለምሳሌ የሕዝብ ድል የተደናቀፈው በወያኔ ግድያና አፈና እርምጃ ብቻ ሳይሆን በተቃዋሚ ነን ባዮች ክህደት መሆኑ ሀቅ ነው:: ወኔ ቢሶች መሪ ተብለው ከመደነቃቸውና ከመታቀፋቸው ባሻገር ታሪካዊ ውጤት ይኖረው የነበረውን የሙት ከተማ አድማ ሁለት ዶክተር ተብዬዎች ከአሜሪካና እንግሊዝ ጋር ሆነው በጠራራ ፀሐይ አክሽፍውታል:: ግለሰቦቹ ግን ዛሬም የተቃውሞ መሪ እየተባሉ ናቸው:: የትግል ታሪካቸው ውዳቂ ሆኖ ሳለ ዛሬም ታጋይና አታጋይ ናቸው ብሎ በስራቸው የሚኮለኮል የለም ማለት አይቻልም:: ወያኔን አምርሮ መቃወም ሲገባ በተለይም ሕዝብን ከፈጀ በኋላ ዓይንህን ለአፈር ማለት ሲጠበቅ ከወያኔ ጋር በየሆቴሉ ውስኪ የሚጨልጡ ተቃዋሚ በሉን ባዮችን ዛሬም መሪያችን የሚሉ አሉ:: አንረባም፣ ወኔውም ቆራጥነቱንም የለም ካሉ በኋላ፣ ዋናው ፍላጎታችን ከወያኔ ጋር መደራደርና መተቃቀፍ ነው ካሉን በኋላ የተቃውሞ መሪ ናቸው ብሎ ማቀፉና ለመከተልም መሰለፍ ከጅልነት በላይ ሀገርን ጎ

ጂ ነው፡፡ በተጨባጭ ሁኔታውም ወንጀልም ሊሆን ይችላል፡፡ የታሪክ ሂደት ማነው ታጋይ የሕዝብ አለኝታ ማነው ከሀዲ ባንዳ የሚለውን ቁልጭ አድርጎ ያሳያል፡፡ መለስ ዜናዊ ለምሳሌ ፀረ ኢትዮጵያ አውሬ መሆኑ ከታወቀ ዘመን አልፏል፡፡ ዛሬ የሚያለቅሱለት ወይ ተገደው ነው ወይ ተጠቀምን ባይ ከርሳሞች ናቸው፡፡ ፀረ ወያኔ ነን ባዮች ቀደምት ወያኔዎች ጉዳይ እዚህ ላይመነሳት አለበት፡፡

ይህንን በተመለከተም በ1997ኡ ምርጫ በቂ ተመክሮና ትምህርት አግኝተን ነበር፡፡ የወያኔ ሽንፈት እውን ሊሆን ሲል ፀረ ወያኔ ነን ያሉት ቀደምት ወያኔዎችና የክልል አንድ ተወላጆች ግልብጥ ብለው ወያኔን ደግፈው ማለትም ዘር ከልጓም ይጠቅሳል ብለው ሲቀሉና አሳፋሪ ሲሆኑ ታዝበናል፡፡ ዛሬም ከወያኔነቱናዘረኛነቱ አልተላቀቀም ብንልም ጀግና ፣ሀገር ወዳድወዘተ በሚል ሲያቀርቡት የነበረው ስዬ አብርሃ በይፋ ወጥቶ ዘረኛ ወያኔነቱን በማረጋገጡ መወናበድን መርጠው የቆዩት ሲንጫጩበት ማዳመጥ ተገደናል፡፡ ስዬና መሰሎቹ ከመለስ ዜናዊ ቢጣሉም ከወያኔነት ቅንጣትም ቅራኔ የላቸውም፡፡ የወያኔን ምስጢር ምስጢራችንም ብለው እስከዛሬ እየጠበቁ ያለት ለዚህም ነው፡፡ ስዬ፣ ገብሩ አስራት÷ ወዘተ የወያኔን ምን ምስጢር አጋለጡ? ጠፉ ስለተባሉ የፖለቲካ እስረኞች ምን አሉ? ምንም! የወንጀል ምስጢር የራሳቸውም ምስጢር ነው፡፡ ዛሬ ስዬ መለስን አዳናቂና ሰፊውን ሕዝብ ሰዳቢ ሆኖ ቢከሰት ስህተቱ እሱን የሚመለከት ሳይሆን ያልሆነውን ሲያወኩ የነበሩትን ይጠቅሳል፡፡ ግለሰቡ ከጥዋቱ የወያኔን ምስጢር ጠባቂ ሆኖ የተገኘ ነው፡፡ ስለ ወያኔ ግፍና ፍጅት፣ ስለወያኔ የግዛት ስርቆትና መስፋፋት ፣ ስለደብዛቸው የጠፉ እስረኞች ትንፍሽም አላለም፡፡ የፖለቲካ እስረኞች አልተያዙም ብሎም ክዷል፡፡ ስዬና መሰሎቹ መለስን ቢጠሉም የትግራይና የወያኔን የበላይነትን ግን ያፈቅራሉ፡፡ እነዚህን ከሕዝብ ጎራ መፈረጅ ወንጀል አይሆንምን? ለነ ስዬ ዘር ከልጓም ብንላቸውም ሳይጠሩት አቤቶች ደግሞ ጥቂት አይደሉም፡፡ በኢትዮጵያ ያሉት የፖለቲካ እስረኞች ከ 100 አይበልጡም ብላ ከዘባረቀች በኋላ ዛሬ መለስ ሞተ ብላ ወይኔ ባይዋም የአሜሪካ ሰልጣኝ ተማሪ ተቃዋሚ ተብዬ አለች፡፡ ትላንት ለቅንጅት ዋና ዘፋኝ የነበሩ

ዛሬ ለመለስ ዜናዊ የሐዘን ዘፈን እየቀረፁ ናቸው:: ትላንት ጨካኝ ፀረ ወያኔ በሉን ብለው የተመፀዳቁ ዛሬ ለመለስና ወያኔ ቡችላ ሀይለማርያም ጊዜ እንስጠው ባይ ሆነዋል:: ቡችላው ግን ከኔ ብዙ አትጠብቁ የመለስን መንገድ እከተላለሁ፤ የታሰሩትም ጋዜጠኞች ሽብርተኞች ናቸው ብሏቸዋል:: ውሀ ቢወቅጡት እንቦጭ!

ይህ በዚህ እንዳለ ግን ከዚህ ቀደም በጣም የተሳሳተ የፖለቲካ ግምጋሜ አድርገውና ደርግን ተራማጅ ብለው ከኅኑ በመሰለፍ ፀረ ሕዝብ ወንጀል የፈፀመ ቡድን መሪዎች ዛሬም ከስህተታቸው አልማር ብለው ለባዕድ ጋዜጠኛ በሰጡት ቃለ መጠይቅ ወያኔ የተረጋጋ ነው፤ መዋቅሩ የጠነከረ ነው፤ ወዘተ ብለው ሲያላዝኑ ተደምጠዋል:: ክህደትም ወኔ ቢስነትም እኮ ልማድ ሊሆን ይችላል? ፋሺስቱን ደርግ ተራማጅ ማለት ፀያፍ ስህተት እንደነበረው ሁሉ ዛሬ ወያኔን ጠንካራና የተረጋጋ ወዘተ ማለቱ ደግሞ ወንጀል ነክ ትግልን አፋኝ ስህተት ነው::

ለሀይለማርያም ደሳለኝ ጊዜ እንስጠው ባይ ቅሌታሞችን ሰውዬው ራሱ ያሳፈራቸው ቢሆንም ( የመለስን ፖለቲካ መስመር ሳላዛንፍ እቀጥላላሁ በማለት) ወራዳነታቸውን ሕዝብ ተገንዝቦ አንቅሮ ሊተፋቸው ይገባል ፤ ይጠበቃል:: ወያኔ ቀውስ ውስጥ ነው -- ስለዚህ ተረጋጋ የሚሉ ዋሾዎች ናቸው:: አቅዋማቸውም ፀረ ሕዝብ ትግል ነውና:: የራሳቸውን ቀቢፀ ተስፋህገራዊ ሊያደርጉ ይጥራሉና:: በወያኔ ውስጥ የተካሄደውና እየተካሄደ ያለውን ቀውሳዊ ሂደት መረዳት ያቃታቸው በዚህ ወያኔ ሊጠናከር ነው ሲሉ በዚያ ግን የገባበትን ረመጥ አንደምታ መቀበልን በተመለከተ ወደ ጎን ይሸኛሉ ::

ዛሬ ወያኔ አገዛዝና ድርጅት ቀውስና ችግር ውስጥ መግባቱ የሚካድ አይደለም :: ይህንን ቀውሱን በማባባስ ለሕዝባዊ ለውጥ መሰረት ማድረግ ሲገባ በባዕዳን ትዕዛዝ መሽመድመዱ ጥፋት ነው:: ተቃዋሚንም መሳቂያ መሳለቂያ ማድረግም የሚያስወግዝ ነው:: ተቃዋሚ ነን እያሉ ግን መሳቂያ የሆኑ ኢምንት ቡድኖች ከመድረኩ መወገድና ማረፍም አለባቸው:: ለነዚህም ሆነ ሕዝብን ሀገር

ን ሲክዱ ለቆዩ ሁሉ ድጋፍ የምንሰጥ ከሆነ ግን ራሳችን በራሳችን ላይ በደልና ግፍን ከማሪ እንሆናለን፡፡ በቂ ተመክሮ አለንና፤ ስንት ውድ ደም ፈሶ የተማርነ ው አለና ይህን ፈረስተን አንጃጃል፡፡ ወዳጅና ጠላትን እንለይ፡፡ ቡከን አድርባ ዩን እንወቅ፡፡ ስህተትን አንድገም፡፡